# በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## በከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ በመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የመጀመሪያ ዲግሪ የትምህርት ጥራት ላይ የሚያደርገውን የክትትልና የግምገማ ተግባርን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ጥር /2008 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ማውጫ

ማውጫ ..................................................i
ክፍል አንድ ..................................................1
መግቢያ ..................................................1
የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ አመሠራረት ..................................................1
የኤጀንሲው ስልጣንና ተግባር ..................................................2
የኤጀንሲው ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል ..................................................3
የኤጀንሲው የፋይናንስ ምንጭ ..................................................4
የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ ..................................................4
የክዋኔ ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ ..................................................4
ለክዋኔ ኦዲት የተለየው የኦዲት አካባቢ (AUDIT AREA) ..................................................5
የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (Audit Issue) እና የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Audit Evaluative Criteria) ..................................................5
የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Audit Evaluative Criteria) ..................................................5
የሥራ ሒደት መግለጫ (Process description)..................................................7
ክፍል ሁለት ..................................................8
ግኝቶች..................................................8
2.1 በከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ" የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የትምህርት ጥራት ተግባርን ለማከናወን የሚያስችል የአሰራር ስርዓት በቁጠባ፣ ብቃት ባለውና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ..................................................8
በመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚሰጡ ትምህርቶች ከአገሪቱ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ፍላጎትና አግባብነት ካላቸው ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ጋር መገናዘባቸውን ማረጋገጥን በተመለከተ..................................................8
በሀገር አቀፍ ደረጃ የተቀረፁትን የትምህርት ፕሮግራሞች (curriculum) በተመለከተ..9

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የመጀመሪያ ዲግሪ ትምህርት የሙያ ብቃት ምዘናን በተመለከተ ........................................ 10
የመንግስት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ የሚኖረው የመማር ማስተማር ሁኔታን በተመለከተ ........................................ 11
በመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ላይ የጥራት ኦዲት መካሄዱን በተመለከተ .. 16
የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የቤተመጽሐፍት እና የቤተሙከራ አገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተ ........................................ 17
ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የሚሰጠው አገልግሎትን በተመለከተ ........................ 19
የተማሪዎችና የመምህራን ምዘናና የምዘና ውጤቶችን በተመለከተ ..................... 20
በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚመደቡ አስተማሪዎች የማስተማር ክህሎት በተመለከተ ........................................ 21
የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጥራትን አስመልክቶ የሚደረግ የጥናትና ምርምር በተመለከተ ........................................ 22
የመንግሥት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መረጃን በተመለከተ ........................ 23
ክፍል ሦስት ........................................ 24
መደምደሚያ ........................................ 24
ክፍል አራት ........................................ 26
የማሻሻያ ሃሳቦች ........................................ 26
አባሪ 1፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርት ........................................ 29
አባሪ ሁለት፡ ድርጅታዊ መዋቅር ........................................ 33
አባሪ 3፡ የሥራ ሂደት መግለጫ ........................................ 34

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. ትምህርት ለአንድ ሀገር ሁለንተናዊ እድገት መሰረት ነው፡፡ በመሆኑም ለዚህ እድገት ብቁ የሰው ኃይል በማፍራት ረገድ ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡ በተለይ ከሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ አኳያ ስንመለከት ከታች ጀምሮ በየደረጃው እየተማረ የመጣውን የሕብረተሰብ ክፍል ወደ ከፍተኛ ትምህርት ሲሸጋገር የሀገሪቱ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጥራት ያለውና ውጤታማ የሆነ ትምህርት እንዲሰጡ ማድረግና ተመርቀው የሚወጡ ዜጎችም ብቃት ያላቸው ሆነው ለሀገር እድገት የተሻለ አስተዋፅኦ የሚያበረክት ትውልድ አድርጎ በመቅረፅ ረገድ የጎላ ሚና አለው ፡፡

2. የከፍተኛ ትምህርት ዘርፎችን እንዲሁም የተቋማትን አግባብና ጥራትን ለማጎልበት ብሎም እውቅና ለመስጠት ተመራቂዎች ከስራው ዓለም ምጣኔ ሀብትና ከማህበረሰቡ ለሚጠበቅባቸው ሁኔታዎች ብቁ እንዲሆኑ ማስቻል የተልኮዖ አንዱ አካል በመሆኑ ኤጀንሲው በአለም አቀፍ የከፍተኛ ትምህርት ስርዓት ደረጃ ያሉ የመማር ማስተማርና ከምርምር ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የጥራትና አግባብነት ሁኔታዎችን መከታተልና ምርጥ ተሞክሮዎችን መለኪያዎችንና ተቀባይነትና አግባብነት ያላቸውን የጥራት መስፈርቶችን ከሌሎች ሀገራት በመውሰድ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጥራት ያለው ውጤታማ ፍትሀዊና አሳታፊ ትምህርት እንዲሰጡ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

## የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ አመሠራረት

3. በኢትዮጵያ የከፍተኛ ትምህርት ሥርዓት ውስጥ አንድ እራሱን የቻለ ሕጋዊ ማእቀፍ ያለው የጥራትና አግባብነት ተቋም በመሆኑ የከፍተኛ ትምህርት ዘርፎችን እንዲሁም የተቋማትን አግባብነትና ጥራት ለማጎልበት ብሎም እውቅና ለመስጠት ሲባል ኤጀንሲው የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 351/1995 ተቋቋመ ፡፡

4. በመቀጠል የአገሪቱ ከፍተኛ ትምህርት በአጠቃላይ በደረሰበት የእድገት ደረጃ ውጤታማ እንዲሆን ሕጋዊ አቅጣጫና አመራር በመሻቱ እና በተለይ በግል ተቋማት የሚሰጡ ከፍተኛ ትምህርት በትምህርት አግባብነት ጥራት የሚጠበቅበትን አወንታዊ አስተዋፅኦ እንዲያበረክት የሚያስችል አቅጣጫን የሚያሲይዝ ስርዓት በማስፈለጉ ኤጀንሲው ከመንግስት የተሰጠውን ተልዕኮ ለማሳካት በድጋሚ በአዋጅ ቁጥር

650/2001 ላይ ሥልጣንና ተግባሩ ከተዘረዘረ በኋላ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 261/2004 እንደገና ተቋቋመ፡፡

## የኤጀንሲው ስልጣንና ተግባር

5. የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ በአዋጅ ቁጥር 650/2001 መሠረት የተሰጡት ሥልጣንና ተግባር፡-

- በግልፅ የሰፈሩ የግምገማና የእውቅና አሰጣጥ መመዘኛዎችንና ስርዓትን በማዘጋጀት በስራ ላይ ያውላል፡፡
- በዚህ አዋጅና ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት ተቋሙን ወይም የተቋሙን ክፍሎች ለመክፈት ወይም ለማሻሻል የሚቀርቡ ፕሮጀክትን በመገምገም ለሚኒስቴሩ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፡፡
- የእውቅና ፈቃድ ወይም እድሳት ለመስጠት የሚያስችል የተቋም ብቃትና የትምህርትና የስልጠና አግባብነትና ጥራት ግምገማን ያካሂዳል፡፡
- የተቋም የትምህርት አግባብነትና ጥራት ማጎልበቻ ስርዓት የከፍተኛ ትምህርት ጥራትን ማረጋገጥ ስለመቻሉ ግምገማ ያካሂዳል፡፡
- በማንኛውም ተቋም የሚሰጡ የከፍተኛ ትምህርትና ስልጠና ከአገሪቱ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ፍላጎትና አግባብነት ካላቸው ፖሊስዎችና ስትራቴጂዎች ጋር መገናዘባቸውን ያረጋግጣል፡፡
- የግምገማ ኮሚቴዎችን ያደራጃል፣ ኃላፊነታቸውና አሰራራቸውን ይወስናል፣ ስራቸውን ሲያከናውኑ የሚከተሉትን የስነ ምግባር መመሪያም ያወጣል፡፡
- በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት ለእውቅና ፈቃድና ለእውቅና ፈቃድ እድሳት የሚቀርቡ ማመልከቻዎችን ይመረምራል ፣ይወስናል፡፡
- የትምህርት አግባብነት ጥራትን ለመገምገም ወይም የእውቅና ፈቃድ ወይም የእውቅና ፈቃድ እድሳት ጥያቄዎችን ለመመርመር አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ አግባብነት ካላቸው አካላት መረጃና አስተያየት ይጠይቃል፡፡
- የትምህርት አግባብነት ጥራት ደረጃዎች መከተላቸውን ለማረጋገጥ ተቋማትን በመገምገም የሚደርስባቸውን የግምገማ ግኝቶች ለትምህርት ሚኒስቴሩ ያቀርባል፡፡
- የተቋማቱን ደረጃ ለመወሰን የሚያስችሉ መመዘኛዎችንና መመሪያዎችን በማዘጋጀት ለትምህርት ሚኒስቴሩ ያቀርባል፡፡

- የተቋማትን መዋሃድ፣ መከፈል፣መዘጋት ወይም የስም ለውጥ አስመልክቶ ለትምህርት ሚኒስቴሩ ምክር ይሰጣል፡፡
- በኢትዮጵያ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ በውጭ አገር የተቋቋሙ ተቋማት ወይም የእነሱ ቅርንጫፎች በተቋቋመባቸው አገሮች እውቅና ያገኙ መሆናቸውንና በዚህ አዋጅና ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች የተቀመጡ የትምህርት አግባብነት ጥራት ደረጃዎችን ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፡፡
- በውጭ ተቋማት የሚሰጡ የትምህርት ፕሮግራሞችና የነዚህን ተቋማት ደረጃና አቋም የሚመለከቱ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ያሰራጫል፡፡
- የከፍተኛ ትምህርት ማስረጃዎች የአቻነት መወሰኛ ስርዓት ያዘጋጃል፤ በውጭ አገር ተቋማት የተሰጡ የትምህርት ማስረጃዎችን የአቻ ግመታ ይሰጣል፡፡
- እውቅና ያገኘ ተቋማትንና ደረጃቸውን፤ ዋና ዋና ክፍሎቻቸውንና የትኩረት መስኮቻቸውን የሚመለከቱ ወቅታዊ መረጃቸውን ይይዛል፤ አግባብነት ባላቸው የመገናኛ ዘዴዎች መረጃዎችን በየጊዜው ለሕዝብ ያሰራጫል

የሚሉት ናቸው፡፡

## የኤጀንሲው ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል

### <u>ድርጅታዊ መዋቅር</u>

6. ኤጀንሲው በአሁኑ ወቅት በአንድ ዋና ዳይሬክተር እና አራት ዳይሬክቶሬት አሉት፡፡ እነሱም የፋይናንስ ግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ፣ እና የሰው ሀብት ስራ አመራርና ልማት ዳይሬክቶሬት፣ የጥራት ኦዲት አቅም ማጎልበት ዳይሬክቶሬት እና የዕውቅና አሰጣጥ፣ አቻ ግመታና የትምህርት ማስረጃ ማረጋገጫ ዳይሬክቶሬት ናቸው፡፡

### <u>የሰው ኃይል</u>

7. ኤጀንሲው ያለው የሰው ኃይል ጥር 30/2008 ዓ.ም ጠቅላላ ብዛት 84 ሠራተኞች ሲሆኑ 37 ሴት እና 47 ወንድ ሰራተኞች በትምህርት ደረጃ ሲተነተን ማስተርስ 24 ባችለር ዲግሪ 17 ፣ ዲፕሎማ 13፣ ሰርተፍኬት 3 ፣ በሌብል ደረጃ 2 ከ9-12 ክፍል 9 እንዲሁም 16 ከ8ኛ ክፍል በታች ናቸው፡፡

## የኤጀንሲው የፋይናንስ ምንጭ

8. የኤጀንሲው ሰራተኞች ደመወዝና እንዲሁም ለሚያከናውናቸው ስራዎች ወጪ መሸፈኛ የሚሆነውን ገንዘብ ዋና ምንጩ በየበጀት ዓመቱ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የሚመደብለት በጀት ነው፡፡ ከ2004 እስከ 2007 ያለው የፋይናንስ አጠቃቀም በሚቀጠለው ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡

| በጀት ዓመት | የተመደበ በጀት | ሥራ ላይ የዋለ | ሥራ ላይ ያልዋለ |
|---|---|---|---|
| 2004 | 5,349,639.00 | 4,683,338.00 | 666,601 (12.4%) |
| 2005 | 6,708,895.00 | 5,914,410.00 | 794,485 (11.8 %) |
| 2006 | 8,461,300.00 | 6,902,338.00 | 1,558,962 (18.45%) |
| 2007 | 10,606,110.00 | 10,298,473.00 | 307,637 (3%) |

የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ

9. የከፍተኛ ትምህርት አግባብነት ኤጀንሲ በመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚሰጡ የመጀመሪያ ዲግሪ የትምህርት ጥራት ላይ የሚያደርገውን የክትትልና የግምገማ ተግባርን ኢኮኖሚያዊ፣ ስኬታማና ብቃት ባለው መልኩ ለማከናወን የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን መገምገም ሲሆን፣ በዚህ ዙሪያ ችግሮች ካሉ በመለየት ችግሮቹን ለማቃለል የሚረዱ የመፍትሄ ሃሳቦችን ለማቅረብ ነው፡፡

## የክዋኔ ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

10. ኦዲቱ በዋነኛነት ያተኮረው በመንግስት ከፍተኛ ትምርርት ተቋማት የሚሰጡ የመጀመሪያ ዲግሪ ፕሮግራሞች ላይ ነው፡፡ ኦዲቱ የሚሸፍነው ከ2004 እስከ 2006 በጀት ዓመታት ድረስ ያለውን የኤጀንሲውን የሥራ ክንውን ሲሆን ኦዲቱ በዋነኛነት የተከናወነው በከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ ሲሆን በናሙና በተመረጡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በደብረማርቆስ እና በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ በናሙና በተመረጡ ኮሌጆቻቸው በመገኘት ሪጃዎችን በመከለስና ለሚመለከታቸው የዩኒቨርሲቲው የትምህርት ጥራት ዳይሬክተሮች፣ ለመምህራን እና ለተማሪዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብና እንዲሁም የመስክ ጉብኝት በማድረግ አሰራሩን በመመልከት ነው፡፡

## ለክዋኔ ኦዲት የተለየው የኦዲት አካባቢ (AUDIT AREA)

11. ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ "በከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ" የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የመጀመሪያ ዲግሪ ፕሮግራም የትምህርት ጥራት ተግባርን ለማከናወን የሚያስችል የአሰራር ስርዓት በቁጠባ፣ ብቃት ባለውና ውጤታማ በሆነ መልኩ የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም የሚል ነው፡፡

## የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (Audit Issue) እና የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Audit Evaluative Criteria)

### <u>የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ</u>

12. ከላይ በተጠቀሰው የኦዲት አካባቢ ሥር ሶስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ተቀምጠዋል፡፡ እነሱም

1. የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጥራትና ደረጃ የጠበቀና ቀጣይነት ያለው መልኩ የመጀመሪያ ዲግሪ ትምህርት እየሰጡ መሆናቸውን እና የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ የክትትል የቁጥጥር ተግባር በብቃት እያከናወኑ መሆኑን መገምገም፤
2. የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ የተጣለባቸውን ኃላፊነት በአግባቡ እንዲወጡ ኤጀንሲው የውስጥ የጥራት ቁጥጥር እንዲያደርጉ አስፈላጊ መረጃ መስጠቱን እና ተቋማት አውቀው ተግባራዊ እንዲያደርጉ አስፈላጊው ድጋፍ ማድረጉን መገምገም፣
3. ኤጀንሲው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ ከውጪም ሆነ የውስጥ ባለድርሻ አካላት ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሠራር ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ የሚሉት ናቸው ፡፡

## የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Audit Evaluative Criteria)

13. ከላይ የተመረጡት ሦስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ለመመዘን የሚረዱ 37 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ የመመዘኛ መስፈርቶች ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑት ከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ የተቋቋመበት አዋጅ፣ ደንብ፤ የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ፣የሥራ መመሪያ እና በኤጀንሲው የተጠናው መሰረታዊ የስራ ሒደት ለውጥ ጥናት፣ የአምስት ዓመት

ስትራቴጂክ እቅድ (2003-2007)፣ (ከ2005-2009) እቅድና የእቅድ ክንውን ከ2004-2006 ፣ መልካም ተሞክሮዎች፣ ኤጀንሲው በመንግስት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የጥራት ኦዲት የተደረጉ ሪፖርቶች ሲሆኑ የተዘጋጁት የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ላይ ስራው የሚመለከታቸው የኤጀንሲው የሥራ ኃላፊዎች አስተያየታቸውን እንዲሰጡበት ቀርቦላቸው አስተያየት እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) በአባሪነት ተያይዟል፡፡

## የሥራ ሒደት መግለጫ (Process description)

14. የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ የጥራት ኦዲትን አስመልክቶ የሚከናወኑ ተግባራት ለማከናወን የዘረጋው የአሰራር ሒደት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ (አባሪ 3 )

**የጥራት ኦዲት የሥራ ሂደት**

- የጥራት ኦዲት የሚደረገው የመንግስትም ሆነ በግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ተቋማዊ የጥራት ኦዲት ከመካሄዱ በፊት እያንዳንዱ ተቋም ራሱን ገምግሞ የግምገማውን ሪፖርት ለከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ ያቀርባል፡፡
- ከዚያም ኤጀንሲው በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ላይ የጥራት ኦዲት ያከናውናል፣
- የጥራት ኦዲት ሪፖርቱን በማዘጋጀትና በማሳተም ኦዲት ለተደረገው ተቋምና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ያሰራጫል፣
- ተቋሙ በጥራት ኦዲቱ ላይ የተመለከቱትን መስተካከል ያለባቸውን ነገሮች ማስተካከል እንዲችል የጥራት ማጎልበቻ እቅድ (Quality Enhancement Plan) እንዲያቀርብ ይደረጋል፣
- ሪፖርቱ በወጣና ለባለድርሻ አካላት በተሰራጨ ከዓመት በኋላ ሌላ የጥራት ኦዲት ቡድን በመሰማራት ተቋሙ ምን ያህል በወጣው ሪፖርት መሰረት መሻሻል እንዳደረገ ይገመግማል፣
- በተደረገው ክትትል መሻሻል ባላደረጉ ተቋማት ላይ ኤጀንሲው አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወስድ ያደርጋል፡፡

# ክፍል ሁለት

## ግኝቶች

### 2.1 በከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ" የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የትምህርት ጥራት ተግባርን ለማከናወን የሚያስችል የአሰራር ስርዓት በቁጠባ፣ ብቃት ባለውና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ

**በመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚሰጡ ትምህርቶች ከአገሪቱ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ፍላጎትና አግባብነት ካላቸው ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ጋር መገናዘባቸውን ማረጋገጥን በተመለከተ**

15. የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚሰጡ ትምህርቶች የአገሪቱን የኢኮኖሚና ማህበራዊ ፍላጎቶችን፣ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን ያገናዘበ እና የምሩቃኖቻቸውን መዳረሻና የቀጣሪዎቻቸውን እርካታ በየጊዜው በማጥናት ከጥናቱ ያገኙትን ግብረ-መልስ እንደ ግብዓት በመጠቀም ሥርዓተ ትምህርታቸውን የሚያጎለብቱበትንና የሚያሻሽሉበትን ስርዓት ዘርግተው ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው፡፡ ኤጀንሲውም ተቋማቱ ሥርዓቱን መዘርጋቱን እና በተዘረጋው ስርዓት መሰረት ተግባራዊ ማድረጋቸውን የሚያረጋግጥበት የአሰራር ስርዓት ሊኖረው ይገባል

16. የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀፅ 89 ተራ ቁጥር 5 መሰረት ኤጀንሲው በማንኛውም ተቋም የሚሰጡ ከፍተኛ ትምህርት እና ስልጠና ከአገሪቱ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ፍላጎትና አግባብነት ካላቸው ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ጋር መገናዘባቸውን ኤጀንሲው ማረጋገጥ ያለበት ቢሆንም በኦዲት ወቅት በደብረማርቆስ፣ በባህርዳር እና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲዎች በተቋማቱ የምሩቃኖቻቸውን መዳረሻና የቀጣሪዎቻቸውን እርካታ በማጥናት ከጥናቱ ያገኙትን ግብረ-መልስ እንደግብዓት በመጠቀም ሥርዓተ ትምህርታቸውን የሚያጎለብቱበትንና የሚያሻሽሉበትን እንዲሁም ለሀገሪቱ ሁለንተናዊ እድገት የሚፈለጉ ብቁ ዜጎችን ማፍራቱን የሚከታተሉበት የአሰራር ስርዓቱ የሌላቸው መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

17. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው የጥራት ኦዲትና አቅም ግንባታ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተጠይቀው ከኤጀንሲው የጥራት ኦዲት አሥር የትኩረት አቅጣጫ (Focus Area) ወስጥ አንዱ መስፈርት መሆኑ፣ ስለዚህ ተቋማት ተመራቂ ተማሪዎቻቸው የት እንዳሉ፣ የተማሩበት ፕሮግራም ምን ያህል ለስራ አለም እንደጠቀማቸው፣ ያጋጠሙዋቸው

ችግሮች ወ.ዘ.ተ. በተመለከተ የክትትል ጥናት /tracer Study/ ማካሄድ ግዴታ እንዳለባቸው ገልጸዋል፡፡ አንዳንድ የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት (ጂማ፣ ጎንደር እና ሀረማያ ዩኒቨርሲቲዎች) የክትትል ጥናቱን አካሂደው ለኤጀንሲው መረጃ እንደላኩ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ነገር ግን ሌሎቹ የመንግስት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የክትትል ጥናት ስለማድረጋቸውና አለማድረጋቸው እንዲሁም ከአገሪቱ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ፍላጎትና አግባብነት ካላቸው ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ጋር የተገናዘቡ ስለመሆናቸው የሚያረጋግጡበት የአሰራር ሥርዓት እንዲኖራቸው ለማስገደድ የሚያስችል የህግ አግባብ እንደሌላቸው በመውጫ ስብሰባ ወቅት ገልጸዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህን በሉ እንጂ አዋጁ አንቀ 89/5 ላይ በግልጽ የተቀመጠ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡ —በአዋጅ በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የመንግስት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚሰጡት ትምህርት ከአገሪቱ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ፍላጎትና አግባብነት ካላቸው ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ጋር መገናዘባቸውን፣ የምሩቃኖቻቸውን መዳረሻና የቀጣሪዎቻቸውን እርካታ በጥናት ተቋማት ማረጋገጣቸውን በየጊዜው ኤጀንሲው አለመከታተሉ፣ ከየተቋማቱ የሚሰጡ ትምህርቶችን ተከታትለው ተመርቀው የሚወጡት ተመራቂዎች ለሀገሪቱ ሁለንተናዊ እድገት የሚፈለጉ ብቁ ዜጎችን ማፍራቱን ማረጋገጥን እና የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ አዳጋች ያደርገዋል፡፡

**በሀገር አቀፍ ደረጃ የተቀረፁትን የትምህርት ፕሮግራሞች (curriculum) በተመለከተ**

18. ኤጀንሲው የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የመጀመሪያ ዲግሪ ትምህርት በሀገር አቀፍ ደረጃ የተቀረፁትን የትምህርት ፕሮግራሞች (curriculum) ተግባራዊ ማድረጋቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች ሲመረቁ ለየትምህርት መስኩ በተቀመጠው ስርዓት መሰረት የንድፈ ሀሳብ ትምህርትና የተግባር ትምህርት አጠናቀው ስለመመረቃቸው ኤጀንሲው የሚያረጋግጥበት አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

19. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት በደብረማርቆስ፣ በባሕርዳር እና በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲዎች የመጀመሪያ ዲግሪ ትምህርት በሀገር አቀፍ ደረጃ የተቀረፁትን የትምህርት ፕሮግራሞች (curriculum) በተሟላ መልኩ ተግባራዊ አለማድረጋቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ፡፡

20. ስለጉዳዩ በደብረማርቆስ፣ በባሕርዳር እና በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲዎች ያሉ የስራ ኃላፊዎች ፣ መምህራን እንዲሁም ተማሪዎች ለቀረበላቸው ጥያቄ ምላሽ ሲሰጡ በተለይ በጤና ሳይንስ ኮሌጆች ላይ የመማር ማስተማር ሒደቱ ካሪኩለሙ ባስቀመጠው ሰዓት መሰረት ኮርሶቹን በተለይ የተግባር ሥልጠናውን መጨረስ አስቸጋሪ እንደሆነባቸው እንዲሁም የመማር ማስተማር ሒደት ተማሪዎች በቂ ክህሎት እንዲሁም በትምህርት ጥራት ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ እንደሚያሳድር ገልፀዋል

21. ስለሁኔታው የኤጀንሲው የጥራት ኦዲትና አቅም ግንባታ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ለቀረበላቸው ጥያቄ ምላሽ ሲሰጡ ኤጀንሲው የጥራት ኦዲት በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ላይ ማካሄድ የውስጥ ጥራት ማጎልበቻ ስርዓት እንዲገነቡ እገዛ ከማድረግና ስርዓቱንም እንደገነቡና እንዳልገነቡ ክትትል ከማድረግ እና ስልጠና ከመስጠት ያለፈ ተማሪዎቻቸውን ለየትምህርት መስኩ በተቀመጠው ስርዓት መሰረት የንድፈ ሀሳብ ትምህርትና የተግባር ትምህርት አጠናቀው ስለመመረቃቸው የሚያረጋግጡበት አሰራር እንዲኖራቸው አስገዳጅ እርምጃዎችን ለመውሰድ የሚያስችል ስርዓት አለመኖሩን ለዚህም የሕግ አግባብ እንደሌላቸው ገልፀዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ በኤጀንሲው መቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር261/2004 አንቀጽ 6/2 የከፍተኛ ትምህርት ምሩቃን ምዘና ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረግ እንዳለበት በግልጽ የተቀመጠ በመሆኑ የሰጡትን ምላሽ አልተቀበልነውም፡

22. ኤጀንሲው የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በሀገር አቀፍ ደረጃ የተቀረፁትን የትምህርት ፕሮግራሞች (curriculum) ተግባራዊ መደረጋቸውን አለማረጋገጡ ካሪኩለሙ ባስቀመጠው ሰዓት መሰረት የንድፈ ሀሳብ ትምህርቱንም ሆነ የተግባር ትምህርት አጠናቀው ስለመመረቃቸው የሚያረጋግጥበት የአሰራር ስርዓት አለመኖሩ ተመራቂዎች ተፈለጊውን ዕቀውቀትና ክህሎት ይዘው መመረቃቸውን ማረጋገጥን አዳጋች አድርጎታል፡፡

**የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የመጀመሪያ ዲግሪ ትምህርት የሙያ ብቃት ምዘናን በተመለከተ**

23. ኤጀንሲው የከፍተኛ ትምህርት ምሩቃን የትምህርት ጊዜቸውን አጠናቀው ሲወጡ ተፈላጊውን ችሎታ መያዛቸውን ለማረጋገጥ የሙያ ብቃት ምዘና የሚያካሂድበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

24. ይሁን እንጂ በኤጀንሲው ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 261/2004 አንቀፅ 6 ተራ ቁጥር 2 መሰረት በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሙያ ብቃት ምዘና የሚያካሄድበትን ስርዓት ይዘረጋል ቢልም ስርዓቱ አለመዘርጋቱ፣ የሙያ ብቃት ምዘናውን የማያረጋግጥ መሆኑ፣ እንዲሁም ምዘናውን ተግባራዊ በማያደርጉ ተቋማት ላይ እርምጃ የማይወስድ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት ተችሏል፡፡

25. ስለጉዳዩ ኤጀንሲው የጥራትና አቅም ግንባታ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተጠይቀው ኤጀንሲው የሙያ ብቃት ምዘና ለማካሄድ አወቃቀሩ አመቺ አለመሆኑን፣ ነገር ግን የሙያ ብቃት እንዲዘጋጅ ከተለያዩ ባለድርሻ አከላት ጋር ተባብሮ በመስራት በህግ እና በጤና ሳይንስ መስክ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምዘና በ2007 እንዲጀመር ተደርጓል፡፡ በቀጣይ በሌሎች የተመረጡ የትምህርት መስኮች ምዘናውን ለማድረግ የኤጀንሲው መዋቅር መስተካከል እንዳለበት ታምኖ የማስተካከሉን ስራ ለመስራት ጥናት እየተደረገ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ልክ እንደጤናውና እንደ ሕግ የትምህርት መስኮች ምዘናውን ማካሄድ ከሚችሉ ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይቶችና ለግምገማው የሚረዱ መስፈርቶችን የማዘጋጀት ስራዎች በ2008 የበጀት ዓመት ለማከናወን ታቅዶ በእቅዱ መሰረት እየተሰራ ነው በማለት ገልፀዋል፡፡ ዳይሬክተሩ ይህን ይበሉ እንጂ ኤጀንሲው ሲቋቋም አደረጃጀቱን በደንብ ቁጥር 261/2004 በተሰጠው ስልጣንና ተግባር መሰረት ሊያዋቅር የሚገባና ኃላፊነቱን መወጣት ይገባው ስለነበረ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል አዳጋች ያደርገዋል፡፡

26. ኤጀንሲው የተመራቂዎችን የሙያ ብቃት ምዘና የሚመዘንበትን ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አለማድረጉ የተመራቂዎችን ብቃት ሆነ በየተቋማቱ የሚሰጠውን ትምህርት ጥረት ለማረጋገጥ አዳጋች ያደርገዋል፡፡

**የመንግስት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ የሚኖረው የመማር ማስተማር ሁኔታን በተመለከተ**

27. ኤጀንሲው፣ በሁሉም የመንግስት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ የሚኖረው የመማር ማስተማር ሁኔታ በክፍል ውስጥም ሆነ በማደሪያ ሥፍራዎች እና በተቋም ግቢዎች ውስጥ ተማሪዎችን ለመማር የሚያበረታታ መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ ለትምህርት አሰጣጥ የሚገለግሉ ቤተሙከራዎች እና ሌሎች መገልገያዎች በተቀመጠው መስፈርት ተግባራዊ መደረጋቸውን መከታተል አለበት፡፡

28. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ የኤጀንሲው የጥራት ኦዲት ሪፖርቶች እንዲሁም በመስክ ኦዲት ወቅት የኦዲት ቡድኑ ተዘዋውሮ ባያቸው ተቋማት የተገኙት ግኝቶች በተለይ 70/30 ተግባራዊ በሚደረግባቸው በምህንድስና፣ በሳይንስና በሕክምና ዘርፎች ያሉ ቤተሙከራ ክፍሎቹ በአብዛኛው ለዘርፉ አስፈላጊ በሆኑ መሳያሪዎች የተደራጁ ባለመሆናቸው ለምሳሌ የሪኤጀንት፣ የኬሚካል፣ የመለዋወጫ እቃ እጥረት ባለበት ሁኔታ የሚከናወን መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

29. በተጨማሪም በመስክ ኦዲት ወቅት በናሙና በታዩት፣ በደብረማርቆስ፣ በባሕርዳር እንዲሁም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲዎች

- በቤተሙከራው የሚመደቡ ተማሪዎች ለየትምህርት ዘርፉ በካሪኩለሙ በተቀመጠው የላብራቶር ንፅፅር ወይም ጥምርታ ጋር የተመጣጣነ አለመሆኑ፣
- በአንድ ጊዜ ሁሉንም ተማሪዎች በማስተናገድ የተግባር ትምህርቱን ለመስጠት ያሉት ክፍሎች ጠባብ በመሆናቸው የአንድ ክፍል ተማሪ በሁለት ዙር ወይም በሶስት ዙር እንደሚከፈሉ እና በአማካይ በአንድ ጠረጴዛ ከ6 -10 ተማሪዎች የሚሰሩ መሆኑ፣

<u>በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ</u>

- የመማር ማስተማር ሒደት የጊዜ አጠቃቀም በወጣው እቅድ መሰረት አለመፈፀሙ፣
- የመምህራን እጥረት በተለይ (በቴክኖሎጂ ዲፓርትመንት) እንዲሁም በአዋላጅ /Midwifer/ የመማሪያ ክፍል ጥበት መኖሩ፣
- የዩኒቨርስቲው ተማሪዎች በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ለመጠቀም የኢንተርኔት አገልግሎት አለመኖር እንዲሁም የኮምፒውተር አቅርቦት በቂ አለመሆን እና ያሉትም ቢሆኑ የተበላሹ እና በአስቸኳይ ጥገና የማይደረግላቸው መሆኑ፣
- የዩኒቨርስቲው መምህራን የየራሳቸው ሎከር፣ ወንበርና ጠረጴዛ፣ መጸዳጃ ፣ መዝናኛ ቦታ በአጠቃላይ ምቹና የተሟላ ቁሳቁስ የሌላቸው መሆኑ፣
- በዩኒቨርሲቲው ከፍተኛ የውሀ ችግር በመኖሩ ምክንያት የመፀዳጃ ቤት፣ መታጠቢያ ክፍሎች እና የመኝታ ክፍሎቹ ጽዳት የሌላቸው መሆኑን፣
- በአንድ የመኝታ ክፍል ውስጥ 4 ተማሪዎች መመደብ ሲኖርባቸው ነገር ግን በአካል ለማረጋገጥ እንደተቻለው 6 -10 ተማሪዎች መሆን እንዲሁም

የተማሪዎች ሎከር በአንድ ክፍል ውስጥ ከተመደቡት ተማሪዎች ጋር የማይመጣጠን መሆኑ፣

- የምግብ መመገቢያ አዳራሹ የምግብ ማብሰያ ክፍሉ ላይ የፍሳሽ ማስወገጃ ቱቦዎች ባለመኖራቸው ከክፍሎቹ የሚወጣው ፍሳሽ በአካባቢው ላይ ከፍተኛ የጽዳት ጉድለት ከማስከተል አልፎ በተማሪው ጤንነት ላይ ችግር እየፈጠረ መሆኑ እንዲሁም ከግቢው የሚወጣው ፍሳሽ አካባቢውን በመበከሉ ከአከባቢው ህብረተሰብ ጋር ግጭት እንዲፈጠር መንስኤ መሆኑ

<u>በባሕርዳር ዩኒቨርሲቲ</u>

- በአንድ የመኝታ ክፍል ውስጥ 4 ተማሪዎች መመደብ ሲኖርባቸው ነገር ግን በአካል ለማረጋገጥ እንደተቻለው 8-12 ተማሪዎች መሆናቸው፣
- የመኝታ ክፍሎቹ ጽዳት በተማሪው በፕሮግራም እንዲያፀዱ በፕሮክተር ቁጥጥር ይደረጋል ቢባልም የመኝታ ክፍሎቹ ጽዳት የሌላቸው መሆኑን
- የተማሪዎች መፀዳጃና መታጠቢያ ክፍሎች ፅዳታቸውን ያልጠበቁ መሆናቸው፣
- በሴቶች የመኝታ ክፍል ያሉት የመታጠቢያ ክፍሎች ፓርትሺን የሌላቸው በመሆኑ በአንድ ጊዜ 10 ተማሪዎች የሚጠቀሙበት መሆኑ፣
- ከወንዶች መጸዳጃና መታጠቢያ ክፍል የሚወጠው ፍሳሽ በአቅራቢያው ያለውን መኝታ ክፍል ውስጥ በመግባት ችግር እያስከተለ መሆኑ፣
- በተማሪዎች መኝታ ክፍሎች የተባይ ማጥፊያ መድኃኒት በወቅቱ ባለመረጨቱ ተማሪው ላይ ችግር እያስከተለ መሆኑ፣
- የተማሪዎች ሎከር በአንድ ክፍል ውስጥ ከተመደቡት ተማሪዎች ጋር የማይመጣጠንና በጋራ እንዲጠቀሙ የተገደዱበትና ቁልፎቹም የአንዱ የሌላውን ሎከር የሚከፍት መሆኑ፣
- የተማሪዎች ህክምና መስጫ በመካከለኛ ክሊኒክ ደረጃ የሚሰጥ አገልግሎት ይሰጣል ቢባልም በመስክ ጉብኝት ወቅት ለማየት የተቻለው ግን ላቦራቶሪው የአይነ ምድር ምርመራ (stool examnation) ብቻ የሚያደርግ መሆኑ፣
- ለተማሪዎች ህክምና አገልግሎት መዋል የሚገባቸው ሁለት አምቡላንሶች ለሌላ አገልግሎት (ለሰርቪስነት፣ ዕቃ ማመላለሻ) መዋላቸው፣

- ኤሌክትሪካል ማሽን ላብ (electrical machine lab) ቤተ-ሙከራው ከተማሪው ቁጥር ጋር አይመጣጠንም በአንድ ክፍል ውስጥ እንኳን 60 ተማሪ ቢኖር 60*6=360 ተማሪዎቸ በሳምንት ያስተናግዳል በተጨማሪም ሰመራ ፣ ደብረታቦር ፣ ወሎ ፣ ደብረማርቆስ ፣ ጎንደር ዩኒቨርስቲዎች ቤተ ሙከራውን ስለሚጠቀሙ ተማሪው ሙከራውን እንኳን ሰርቶ ለማቅረብ በቂ ጊዜ የማያገኝ መሆኑ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ዋናው ግቢ

- የተመደቡ ሴት ተማሪዎች በሁለት ሰፊ ክፍል (Open Room) ውስጥ 40 እና 56 ተማሪዎች በአንድ ላይ የሚያድሩበት ሁኔታ መኖሩ ክፍሎች ፓርትሺን የሌላቸው እንዲሁም በቂ ሎከር እና የመኝታ ክፍሉ ቁልፍ የሌላቸው መሆኑ
- የተማሪዎች ፋርማሲ ጊዜው ያለፈባቸውን መድሐኒቶች በፍጥነት የሚወገዱበት ስርዓት ባለመኖሩ ፋርማሲው የቦታ ጥበት መኖሩ፣

የጤና ሳይንስ ኮሌጅ የነርሲንግ እና የአዋላጅ ትምህርት ቤት

- ሰፈረ ሰላም ነርሲንግ ት/ቤት ለተመደቡ ተማሪዎቹ የመኝታ አገልግሎት እየሰጠ ቢሆንም ገና በመደራጀት ላይ ያለ በመሆኑ የቤተሙከራ ትምህርቱን በተለያዩ ቦታዎች (የ 1ኛ ዓመት ነርሲነግ እና አዋላጅ ተማሪዎች ዘውዲቱ ሆስፒታል፣ 2ኛ ዓመት ተማሪዎች በቅዱስ ጳውሎስ እንዲሁም 3ኛ አመት ተማሪዎች በጥቁር አንበሳ የነርሲነግ ትምህርት ቤት ውስጥ ዩማስተማር ሒደት ይከናወናል ነገር ግን ተማሪዎቹ ንድፈ ሀሳብ የሚማሩበት እና የተግባር ትምህርቱ የሚሰጥበት ቦታ የተራራቀ በመሆኑ ምክንያት እንዲሁም ባለው የትራንስፖርት ችግር ምክንያት የትምህርት ሒደቱ የሚያመልጣቸው መሆኑ፣ አስተማሪዎቹም በትራንስፖርት እጦት ምክንያት በሰዓት መድረስ ባለመቻላቸው የትምህርት መርሀ ግብሩ ሰዓት የሚሸራረፍ መሆኑ፣

የጤና ሳይንስ ኮሌጅ የፋርማሲ ትምህርት ቤት በተመለከተ

- በካሪኩለሙ መሰረት አንድ ሴሚስተር 16 ሳምንት ያለው ሲሆን የተቀመጠውን ሳምንት በተለያዩ ምክንያቶች ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ የማይደረግ መሆኑ እና አብዛኛውን ጊዜ 13 ሳምንት ብቻ መሆኑ፣ ከዚህ

ውስጥ 11 ሙከራዎች (Experment) መስራት ሲገባቸው ሰርተው የሚወጡት 7 ወይም 8 ብቻ መሆኑ፣

- የተማሪዎች መማሪያ ክፍሎች፣ የመኝታ ክፍሎች እንዲሁም ላይብራሪ ካለው ተማሪ ቁጥር ጋር ያልጠመጣጠኑ መሆናቸው፣
- ላቦራቶሪዎች ውስጥ ያሉ ከፍተኛ ወጪ የወጣባቸው መሳሪያዎች ቢኖሩም በክህሎት ክፍተት ምክንያት አገልግሎት እየሰጡ አለመሆኑ፣
- የላቦራቶሪው ኬሚካል ፈሳሽ ተረፈ ምርት የአወጋገድ ስርዓት ስለሌለው እዛው ላቦራቶሪ ውስጥ ባለው የእጅ መታጠቢያ ሲንክ ላይ የሚፈሱ መሆኑ፣
- ላቦራቶሪ የተደረጉት ክፍሎች መጀመሪያውኑ ለዚሁ ታስበው የተገነቡ አለመሆናቸው፣

30. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው የጥራት ኦዲትና አቅም ግንባታ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተጠይቀው ምላሽ ሲሰጡ በመጀመሪያ የመንግስት ተቋማት የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ መሰረት አካዳሚያዊ ኦዲት ማከናወንና ድክመታቸውን ማሻሻል በጥንካሬያቸው ላይም የበለጠ መስራት ከዚህም በተጨማሪ የግምገማውን ውጤት ለኤጀንሲው መላክ ይገባቸዋል፡፡ የኤጀንሲውም መማር ማስተማር ሁኔታ በክፍል ውስጥም ሆነ በተቋም ግቢዎች ውስጥ ተማሪዎችን ለመማር የሚያበረታታ መሆኑን በጥራት ኦዲት ወቅት የሚታይ ሲሆን ኤጀንሲው የሚሰራው ስራ ተቋማቱ የውስጥ ጥራት ማጎልበቻ ስርዓት እንዲገነቡ እገዛ ከማድረግና ስርዓቱንም እንደገነቡና እንዳልገነቡ ክትትል ከማድረግ እና ስልጠና ከመስጠት ያለፈ የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚቋቋሙት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ መሰረት በመሆኑ ኤጀንሲው እውቅና ስለማይሰጣቸው ተጠያቂ የሚሆኑበት አሰራር አልተዘረጋም ሲሉ ገልፀዋል፡፡ የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀፅ 41 ተራ ቁጥር 2 በማንኛውም የመንግስት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ በክፍል ውስጥም ሆነ በተቋም ግቢዎች ውስጥ ተማሪዎችን ለመማር የሚያበረታታ መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል ብሎ በግልጽ ስለሚደነግግ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል አዳጋች ያደርገዋል፡፡

31. ተማሪዎች በክፍል ውስጥ፣ በቤተ ሙከራ ሆነ በማደሪያ ሥፍራዎች እና በተቋም ግቢዎች ውስጥ ምቹ ሁኔታዎች ተመቻችቶላቸው የመማር ማስተማር ሒደትን እንዲከታተሉ አለመደረጉ በትምህርት ጥራት ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ከማሳደሩም

በላይ ተማሪው በቂ እውቀት እንዳያገኝ መምህራኑም ጥራት ያለው ትምህርት እንዳይሰጡ ያደርጋል፡፡

**በመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ላይ የጥራት ኦዲት መካሄዱን በተመለከተ**

32. ኤጀንሲው በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ላይ የጥራት ኦዲት ሊያካሂድ ይገባል፡፡ የጥራት ኦዲት ወቅት የሰጠውን የመፍትሄ ሀሳቦች እና ማሻሻያዎች ተቋማት ተግባራዊ ማድረጋቸውን የሚከታተልበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ በተጨማሪም እያንዳንዱ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የትምህርት ጥራትን የሚከታተል አቋቁሞ ተግባራዊ ማድረጋቸውን ኤጀንሲው ማረጋገጥ አለበት፡፡

33. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በባሕርዳር (እ.ኤ.አ. 2008)፣ በአዲ አበባ ዩኒቨርሲቲ (እ.ኤ.አ. 2009) እና በደብረማርቆስ (እ.ኤ.አ. 2014) ዩኒቨርሲቲዎች ኤጀንሲው የጥራት ኦዲት አድርጓል፡፡ ነገር ግን በዩኒቨርሲቲዎች ላይ በጥራት ኦዲት የተገኙ ግኝቶች ላይ ማስተካከያ ማድረጋቸውን የጥራት ማጎልበቻ (Quality Enhancement Plan) ፕላን አዘጋጅተው ተቋማቱ ለኤጀንሲው ቢላክም በጥራት ኦዲት ወቅት የተገኙ ግኝቶች በአብዛኛው ችግሮቹ ያልተቀረፉ መሆናቸውን በመስክ ጉብኝት ወቅት እና ከተከለሱ መረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡ እንዲሁም ኤጀንሲው በሁሉም በግል እና በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ላይ የጥራት ኦዲት ማከናወን ያለበት ሲሆን ከ2001- 2007 ዓ.ም በሰባት ዓመት ውስጥ የጥራት ኦዲት ያደረገው 54 ሲሆን 19 የመንግስት እና 46 የግል ተቋማት መሆኑ አብዛኛው የመንግስት ተቋማት ላይ ትኩረት አድርጎ የጥራት ኦዲት አልተካሄደም

34. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው የጥራት ኦዲትና አቅም ግንባታ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተጠይቀው በመንግስትም ሆነ በግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ላይ የጥራት ኦዲት ካከናወነ በኋላ ሪፖርቱን አሳትሞ ኦዲት ለተደረገው ተቋምና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ያሰራጫል፡፡ እያንዳንዱ ኦዲት የተደረገ ተቋሙ በጥራት ኦዲቱ ላይ የተመለከቱትን መስተካከል ያለባቸውን ነገሮች ማስተካከል እንዲችል የጥራት ማጎልበቻ እቅድ (Quality Enhancement Plan) እንዲያቀርብ የሚደረግ ሲሆን አብዛኞቹ የጥራት ኦዲት የተደረገባቸው ተቋማት ይህንን እቅድ አዘጋጅተው አቅርበዋል፡፡ በዚህ መሰረት ሪፖርቱ ከወጣ ከዓመት በኋላ ሌላ የጥራት ኦዲት ቡድን በመሰማራት ተቋሙ ምን ያህል በወጣው ሪፖርት መሰረት መሻሻል እንዳደረገ የሚገመግም ቢሆንም ኤጀንሲው

እስካሁን በተደረገው ክትትል መሻሻል ባላደረጉ የመንግስት ተቋማት ላይ ምንም እርምጃ እየወሰደ አይደለም፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁ.650/2009 አንቀጽ 5 መሰረት የሚቋቋሙት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ መሰረት በመሆኑና ኤጀንሲው እውቅና ስለማይሰጣቸው ተጠያቂ የሚሆኑበት አሰራር አልተዘረጋም በማለት ገልፀዋል፡፡ ዳይሬክተሩ ይህን ይበሉ እንጂ የጥራት ማስከበር ሥራ ለዕውቅና ብቻ ሳይሆን ከዜጎች ማፍራት ጋር የተያያዘ ስለሆነና ክፍተቱ አለመደፈኑን ለሚመለከተው አካል በማሳወቅ ማስተካከያ እንዲደረግ ማስገደድ ይቻል ስለነበረ የተሰጠውን መልስ አልተቀበልነውም፡፡

35. የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀፅ 22 ተራ ቁጥር 5 የመንግስት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጥራት ማጎልበትን አስመልክቶ መውሰድ ስለሚገባቸው እርምጃዎች በጥራት ኦዲት ላይ የተሰጡ ማሻሻያዎች እንዲተገብሩ አለመደረጉ የሚያፈራቸው ዜጎች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ከማሳደሩም በላይ ከፍተኛ የሰው ኃይልና ሀብት ወጥቶበት የተከናወነውን ኦዲት ትርጉም አልባ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

**የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የቤተመጽሐፍት እና የቤተሙከራ አገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተ**

36. በሁሉም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የቤተመጽሐፍት እና የቤተሙከራ አገልግሎት ደረጃውን የጠበቀ እና ከተማሪው ቁጥር ጋር የተመጣጠነ ሊኖር ይገባል፡፡ ኤጀንሲውም ያወጣው የተማሪ እና የቤተመጽሀፍት ሆነ የቤተሙከራ ንጽጽር በሚፈለጌ ደረጃ አቅርቦት መኖሩን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

37. በኦዲት ወቅት በናሙና በታዩት በደብረማርቆስ፣ ባሕርዳር እና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲዎች በተፈጥሮ እና ኮምፒተሽናል ሳይንስ ኮሌጅ፣ በቴክኖሎጂ ኮሌጅ፣ በጤና ሳይንስ ኮሌጅ ያሉ ቤተመፅሀፍት መፅሐፍቶች ተማሪዎች የሚፈልጓቸው የመማሪያ መፅሐፍቶች ጋር ያልተመጣጠነ መሆን፣ የአንዳንድ መፅሐፍቶች ገፅ የተገነጣጠለ መሆኑ፣ መምህራኖች ተማሪዎቹ እንዲያነቡያቸው የሚሰጡት ዋቢ መጽሐፎች (Reference book) በዩኒቨርሲቲው ላይብረሪዎች ውስጥ አለመኖራቸውን፣ ለኢ-ላይብራሪ የሚረዳ ኮምፒውተር ከተማሪው ቁጥር ጋር ያልተመጣጠነ መሆንና በአብዛኛው በኔትወርክ ችግር ብዙ ጊዜ አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑን እንዲሁም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተፈጥሮ ሳይንስ ኮሌጅ ዋናው ቤተመፅሐፍት እና የባሕርዳር

ዩኒቨርሲቲ ቤተመጽሃፍት ቤቶች በየጊዜው ጥገና ስለማይደረግለት ዝናብ በዘነበ ቁጥር ፍሳሹ መጽሃፍቶችን እያበላሸ መሆኑ ለመረዳት ተችሏል ፡፡

38. በተጨማሪም አብዛኛዎቹ ቤተሙከራዎች ለአስተማሪዎችም ሆነ ሙከራ ለሚያደርጉ ተማሪዎች የተሟላ አልባሳትና መከላከያ መሳሪያዎች አለመኖር ፣ በአብዛኛው የእሳት መከላከያ ማጥፊያ (Fire Distingusher) የሌላቸው መሆኑ ፣ በየዓመቱ የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች የሚቀበሉት የተማሪዎች ብዛት እና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማቱ ከሚገኙት አንዳንድ የግብአት ማለትም የቤተ ሙከራ መገልገያ መሳሪያዎች፣ መማሪያ ክፍሎች፣ መጽሀፍት ወ.ዘ.ተ. ጋር አለመመጣጠን ከፍተኛ የጥራት መጓደል እያስከተለ እንደሆነ መጠይቁ የቀረበላቸው የየተቋማቱ የስራ ኃላፊዎች፣ መምህራን እንዲሁም ተማሪዎች ገልፀዋል፡፡

39. የኤጀንሲው የጥራት ኦዲትና አቅም ግንባታ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በሰጡት ምላሽ ጥራትን ለማስጠበቅ የግብዓት- ሂደት- ውጤት ጥራት መጠበቅ ግዴታ ነው፡፡ አሁን ያለው ሁኔታ በየዓመቱ የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች የሚቀበሉት የተማሪዎች ብዛት እና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማቱ ከሚገኙት አንዳንድ የግብአት ማለትም የቤተ ሙከራ መገልገያ መሳሪያዎች፣ መመማሪያ ክፍሎች፣ መጽሀፍት ወ.ዘ.ተ. ጋር አለመመጣጠን ከፍተኛ የጥራት መጓደል ሊያስከትል እንደሚችል እናውቃለን፡፡ ሆኖም ግን ኤጀንሲው ያለውን ሁኔታ በጥራት ኦዲት በመገምገም ተቋማት እንዴት የውስጥ ጥራት ማስጠበቂያ ስርዓት መገንባት እንዳለባቸው አስተያየቶችን መስጠት ነው፡፡ የተቋሞቹ የውስጥ ጥራት ማጎልበት ሲጎለብት እነዚህ ሁሉ ችግሮች ይቀረፋሉ ብለን እናምናለን በማለት ገልፀዋል፡፡ ኃላፊው ይህን ይበሉ እንጂ በየከፍተኛ ትምህርቱ አስፈላጊው ግብአቶች ተሟልተው ትምህርት እየተሰጠ መሆኑን ኤጀንሲው ማረጋገጥ ስላለበት የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

40. በሁሉም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በቤተ መጽሐፍት አገልግሎት ከተማሪው ቁጥር ጋር የተመጣጠነና የሚፈለጉ መፅሐፎች የማይገኙ ከሆነ መሆኑ፣ እና የቤተሙከራ አገልግሎት ከሚማረው ተማሪዎች ንጽጽር ጋር የተመጣጠነ ካልሆነ እንዲሁም በቤተሙከራዎች ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በቲዎሪ የተማሩትን በቀላሉ ወደ ትግበራ ለመቀየር የሚያስችል የተሟላ የቤተ ሙከራ አገልግሎት የማያገኙ ከሆነ የሚፈለገውን ዕውቀት እና ክህሎት ሳይጨበጡ እንዲመረቁ ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡

**ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የሚሰጠው አገልግሎትን በተመለከተ**

41. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚሰጡ አገልግሎቶች (የተቋሞች ሕንፃ ዲዛይን የግቢዎቻቸው ተፈጥሯዊ አቀማመጥ ኮምፒውተሮቻቸው) እና ሌሎች የመገልገያ አውታሮቻቸው ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ፍላጎታቸውን ግምት ውሰጥ ያስገባ ሊሆን ይገባል፡፡ ኤጀንሲው ደግሞ ተቋማቱ የሚሰጡት አገልግሎት ለአካል ጉዳተኞች አመቺ ሁኔታ መመቻቸቱን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

42. የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀፅ 40 ተራ ቁጥር 3 የተቋሞች ሕንፃ ዲዛይን የግቢዎቻቸው ተፈጥሯዊ አቀማመጥ ኮምፒውተሮቻቸውና ሌሎች የመገልገያ አውታሮቻቸው የተማሪዎች ፍላጎት ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን እንዳለበት ቢደነግግም በአዳዲስ የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሲሰሩም እና የነባሮቹ የማስፋፊያ ግንባታዎች በአንዳንድ ተቋማት ሲከናወኑ የደረጃ መውጫ መንገድ ከመሰራቱ በስተቀር በሌሎች አገልግሎቶች ላይ ትኩረት ያልተሰጠው መሆኑ በመስክ ኦዲቱ ወቅት በተደረገ ጉብኝት እና መጠይቁ ከቀረበላቸው ኃላፊዎች እንዲሁም በናሙና መጠይቅ የቀረበላቸው የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

43. ስለሁኔታው የኤጀንሲው የጥራት ኦዲትና አቅም ግንባታ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ከሌሎች ወንድሞቻቸውና እህቶቻቸው እኩል ከትምህርት ስርዓቱ ተጠቃሚ መሆን እንዳለባቸው በማመን ተቋማት የጥራት ኦዲት የሚደረጉበትን መስፈርት በማሻሻል የከፍተኛ ትምህርት ለመማር ማስተማሩ የተዘጋጁ ቁሳቁሶች ለአካል ጉዳተኞች ተስማሚ በሆነ መንገድ መዘጋጀት እንዳለባቸው የማሻሻያ ሃሳብ መሰጠቱን፣ በጥራት ኦዲት ግምገማው መሰረትም ተቋማቱ አስፈላጊውን ማሻሻያ እርምጃ መውሰድ ይጠበቅባቸዋል በማለት ገልፀዋል ፡፡

44. በመስክ ኦዲት ወቅት ካየናቸው ዩኒቨርሲቲዎች መካከል የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተሻለ አገልግሎት እየሰጠ ቢሆንም በደብረማርቆስ፣ ባሕርዳር ዩኒቨርሲቲ ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የሚሰጠው አገልግሎት በአንዳንድ ተቋማት የደረጃ መውጫ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚገነቡዋቸው መሠረተ ልማቶች እና የአገልግሎት መስጫዎች የአካል ጉዳተኞችን ተጨባጭ ሁኔታ ግምት ውስጥ አለማስገባቱ ሁሉም ዜጎች በእኩል ሁኔታ በመማር ማስተሩ ሂደቱ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ የሚያደርግ እና በትምህርት ጥራቱ ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡

**የተማሪዎችና የመምህራን ምዘናና የምዘና ውጤቶችን በተመለከተ**

45. በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ መምህራን የተማሪዎቻቸውን ችሎታ በአካዳሚክ ውጤታቸው መሠረት ብቻ ሊመዝኑ ይገባል፡፡ እንዲሁም የመምህራኑን በመማር ማስተማር ሂደት ላይ የነበረውን አፈጻጸም ተማሪዎች በመምህራኑ ምዘና የሚሳተፉበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ በተማሪዎቹ ምዘና መሰረትም ለመምህራኑ ግብረ መልስ ሊሰጥ ይገባል፡፡ ኤጀንሲው የተማሪዎች ምዘናና የምዘና ውጤቶችን አስመልክተው በተማሪዎችም ሆነ በአስተማሪዎች የሚቀርቡ ቅሬታዎች ትኩረት ተሠጥቷቸው በጥንቃቄና በአፋጣኝ መፍትሔ መሰጠቱን ሊያረጋግጥ ይገባል፤፤

46. በመስክ ኦዲት ወቅት በናሙና በታዩ በደብረማርቆስ፣ ባሕርዳር እንዲሁም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲዎች የተማሪዎች በአካዳሚክ ውጤታቸው መሰረት የሚደረግ ምዘናና አስተማሪዎች በተማሪዎች የሚመዘኑበት የአሰራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉ ታውቋል፡፡ነገር ግን የተማሪዎች በተሰጠው ምዘና ላይ የሚያቀርቡት ቅሬታዎች የሚስተናገዱበት የተሻለ ሥርዓት የተዘረጋ ቢሆንም መምህራን በተማሪዎች የሚሰጣቸውን ምዘና ላይ የሚያቀርቡት ቅሬታ ግን የሚስተናገድበት ሥርዓት አለመኖሩ በናሙና ያነጋገርናቸው መምህራን ገልጸዋል፡፡

መምህራኑ ተማሪዎች ፍትሃዊ በሆነ መልኩ ተማሪዎቹ መምህራኖቹን ይመዝናሉ ብለው እንደማያምኑ ገልጸው ምክንያቱም ተማሪዎቹ ምዘናውን የሚያከናውኑት ከመምህራኑ ከማስተማር ብቃት ጋር አያይዘው ሳይሆን ከአስመዘገቡት የአካዳሚክ ውጤት ጋር አያይዘው መሆኑን፣ በዚህም አነስተኛ የምዘና ውጤት ላለማግኘት አስተማሪዎች ለተማሪዎች የፈተና ውጤት ሲሰጡ አነስተኛ ውጤት ላስመዘገቡ ተማሪዎች ባመጡት የፈተና ነጥብ (በአካዳሚክ ውጤታቸው) ሳይሆን በተማሪዎች ምዘና ወቅት አነስተኛ ነጥብ ላለማግኘት ወይም አላባቃችሁም ተብለው ድጋሚ አስተምረው ላለመፈተን በሚል መንፈስ መሆኑን በናሙና መጠይቅ የቀረበላቸው መምህራን ገልፀዋል፡፡

47. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው የጥራት ኦዲትና አቅም ግንባታ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተጠይቀው ከጥራት ኦዲት መስፈርቶች አንዱ የመምህራን ምዘና ተገቢ ሚዛናዊና ግልጽ በሆነ መንገድ እንዲከናወን የሚጠይቅ ሲሆን መስፈርቶች በትክክል እንዲተገበሩ የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ኦዲት በማድረግ በጥራት ኦዲት በማከናወን አስፈላጊውን መሻሻል የሚደረግ መሆን ገልጸዋል፡፡

48. የመምህራን በምዘና ወቅት አነስተኛ ነጥብ ላለማግኘት እና ድጋሚ ላለመፈተን ተብሎ ትክክለኛ የተማሪውን የአካዳሚክ ውጤት አለመግለጽ ተመርቀው በሚወጡ ተማሪዎች ብቃት ላይ የራሱን አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡

**በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚመደቡ አስተማሪዎች የማስተማር ክህሎት በተመለከተ**

49. በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚመደቡ አስተማሪዎች ከአካዳሚክ ክህሎታቸው ባሻገር የማስተማር ክህሎት እንዲኖራቸው ሥራ ከመጀመራቸው በፊትም ሆነ በሥራ ላይ ተገቢው ሥልጠና ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ እንዲዳብር በየከፍተኛ ትምህርት ተቋማቱ የሚያስተምሩ መምህራንም የማስተማር ስልጠና ወሰዱ መሆናቸውን በየተቋሞች መሰጠቱን ኤጀንሲው ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

50. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ባነጋገርናቸው በደብረማርቆስ፣ ባሕርዳር እንዲሁም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲዎች የሚያስተምሩ መምህራን የማስተማር ክህሎታቸው እንዲዳብር በተለይ በቤተሙከራ የአዳዲስ መሳሪያዎች እንዲሁም ያሉትንም ቢሆን በአግባቡ ለመጠቀም በቂ እና ወቅታዊ ስልጠና እየተሰጣቸው እንዳልሆነ ገልፀዋል፡፡ ኤጀንሲው በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚመደቡ አስተማሪዎች ከአካዳሚክ ብቃታቸው በተጨማሪ የማስተማር ክህሎታቸው እንዲዳብር የማስተማር ክህሎት ስልጠና በተቋሞች መሰጠቱን እንዲያረጋግጥ የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ኃላፊነት ቢሰጠውም ይህ መሆኑን እያረጋገጠ አለመሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

51. ስለጉዳዩ  የኤጀንሲው የጥራት ኦዲትና አቅም ግንባታ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተጠይቀው በኤጀንሲ የጥራት መገምገሚያ መስፈርቶች መሰረት ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ ለመምህራን የማስተማር ክህሎታቸው እንዲዳብር ስልጠና መሰጠቱን ማረጋገጥ መሆኑን ገልጸው አብዛኞቹ የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በዚህ መሰረት በጀት ይዘው ለአካዳሚክ ስታፍ ስልጠና የአጭር ጊዜና የረጅም ጊዜ ስልጠና እንደሚሰጡ፣ በቤተሙከራ የአዳዲስ መሳሪያዎችን አጠቃቀም በተመለከተ የሚሰጥ ስልጠና ግን ለአካዳሚክ ስታፉ ከሚሰጠው ስልጠና ጋር ሲነጻጸር ግን በጣም አነስተኛ መሆኑን በጥራት ኦዲት ወቅት መረዳታቸውን ገልጸዋል፡፡ ነው፡፡ ስለዚህ ኤጀንሲው ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ጥራት ማስጠበቂያ ስርዓት ግንባታ በተገቢው ሁኔታ እንዲያካሂዱና አስፈላጊውን መሻሻል እንዲያደርጉ የማሻሻያ ሃሳብ

መስጠታቸውን ገልፀዋል፡፡ መምህራኑ የማስተማር ክህሎት ማግኘት አለማግኘታቸውን ኤጀንሲው ስለማረጋገጡ ግን ምላሽ አልሰጡም፡፡

52. ኤጀንሲው በተቋማት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራኖቻቸው የማስተማር ክህሎት እንዲገኙ ካልተደረገ እና ይህ ክህሎት የሚዳብርበት ተከታታይ ስልጠና ካላገኙ፣ እንዲሁም በላብራቶሪ ቴክኒሺያንነት ለሚሰሩ በተለይም በቤተሙከራ ያሉትንም ሆነ በተለያየ ጊዜ የሚመጡ የአዳዲስ መሳሪያዎችን አጠቃቀም አስመልክቶ ተከታታይ ስልጠና ካላገኙ ያላቸውን ዕውቀትና ክህሎት ለተማሪዎቻቸው በተገቢው መንገድ እንዳያስተላልፉ ያደርጋቸዋል፡፡

## የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጥራትን አስመልክቶ የሚደረግ የጥናትና ምርምር በተመለከተ

53. ኤጀንሲው የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጥራትን በተመለከተ ጥናትና ምርምር ሊያከናውን ይገባል፡፡ በተጨማሪም ሌሎች ተቋማትና አካላት ትምህርትና ምርምር አስመልክተው የሚከናወኑ የጥናትና ምርምር መረጃዎችን ሊያሰባስብ እና በማቀናበር ለሚመለከታቸው ተቋማት ሊያሰራጭ ይገባል፡፡

54. ነገር ግን ኤጀንሲው የትምህርትና ስልጠና ዘርፍ የቀጣዩ አምስት ዓመታት ዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ 2003-2007 ላይ የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጥራትን በተመለከተ የሚከናወኑ የጥናትና ምርምር መረጃዎችን በመሰብሰብና በማቀናበር ለሚመለከታቸው ተቋማት እንደሚያሰራጭ በእቅዱ የያዘ ቢሆንም በእቅዱ መሰረት ያላደረገ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

55. ስለጉዳዩ የኤጀንሲው ኃላፊዎች ተጠይቀው የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጥራትን በተመለከተ የጥናትና ምርምር ሥራ እስካሁን አለመሰራቱን፣ በሌሎች የተከናወኑትም መረጃዎችም ያልተሰበሰቡ መሆኑን ለኦዲት መመዘኛ መስፈርቱ በሰጡት ምላሽ ላይ ገልፀዋል፡፡

56. ኤጀንሲው የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጥራትን በተመለከተ ጥናትና ምርምር አለማድረጉ እንዲሁም በመስኩ የሚደረጉ ጥናቶችና ምርምሮችን እየተከታተለ አለመሰብሰቡ የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል ለሚደረጉ የፖሊሲና ስትራቴጂ ላይ የራሱን አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡

***የመንግሥት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መረጃን በተመለከተ***

57. ***ኤጀንሲው የመንግሥት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መረጃን በዳታቤዝ አደራጅቶ ሊይዝ ይገባል፡፡ የተያዙትም መረጃዎች በየጊዜው ወቅታዊ ሊደረጉ እና መረጃዎቹን ለሚፈለጉ አካላት በሙሉ የሚያገኙበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ በየካታጎሪ በመያዝ መረጃው በሚፈለግበት ጊዜ በቀላሉ ለማግኘት የሚያስችል ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡***

58. ***ይሁን እንጂ ኤጀንሲው የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚመለከቱ መረጃ አጠናቅሮ የማይዝ መሆኑ እንዲሁም ከባለድርሻ አካላት ጋር በቴክኖሎጅ የታገዘ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ እያደረገ አለመሆኑን በኦዲቱ ወቅት እና የኤጀንሲው ኃላፊዎች የመንግስት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትን የሚመለከቱ መረጃዎችን እንዳልተያዘ ለኦዲት መመዘኛ መሰፈርት በሰጡት አስተያየት ላይ ገልጸዋል፡፡***

59. ***ስለጉዳዩ የኤጀንሲው ኃላፊዎች መረጃው ለምን እንዳልተያዘ ተጠይቀው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የግል የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን የሚመለከት መረጃ መያዝ የጀመሩ መሆኑን የመንግስትን ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚመለከቱ መረጃዎን እንደማይዙ በመውጫ ስብሰባ ወቅት በቃል ገልጸዋል፡፡***

60. ***ኤጀንሲው የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን መረጃዎችን አጠናቅሮ አለመያዙ ስለተቋማቱ የሚፈለጉ መረጃዎችን የሚፈልጉ አካላት በቀላሉ እንዳያገኙ ከማድረጉም በላይ በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ መስጠትን አዳጋች ያደርገዋል፡፡***

## ክፍል ሦስት

## መደምደሚያ

61. ኤጀንሲው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የትምህርት ጥራት ተግባርን ለማከናወን የአሰራር ስርዓት በቁጠባ፣ ብቃት ባለውና ውጤታማ መሆኑ ሲገመገም የሚከተሉት ዋና ዋና ግድፈቶች ተገኝተዋል፡-

- ኤጀንሲው የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የምሩቃኖቻቸውን መዳረሻና የቀጣሪዎቻቸውን እርካታ በተመለከተ ክትትል ማድረጋቸውን ተገቢው ክትትል የማይደረግ መሆኑ፣ እንዲሁም ለሀገሪቱ ሁለንተናዊ እድገት የሚፈለጉ ብቁ ዜጎችን ማፍራቱን እና የሚሰጡ ትምህርቶች አግባብነት ካላቸው ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች የተገናዘቡ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚከታተልበት የአሰራር ስርዓት የሌለው መሆኑ፣
- ኤጀንሲው የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የመጀመሪያ ዲግሪ ትምህርት በሀገር አቀፍ ደረጃ የተቀረፁትን የትምህርት ፕሮግራሞች (curriculum) መሰረት ተገቢውን የንድፈ ሀሳብ ትምህርቱንም ሆነ የተግባር ትምህርት አጠናቀው በተተመነው ሰዓት መሰረት ተምረው መመረቃቸውን የሚረጋግጥበት አሠራር አለመኖሩ፣
- ኤጀንሲው በተሰጠው ስልጣንና ተግባር መሰረት በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተመርቀው የሚወጡ ተማሪዎችን የሙያ ብቃት ምዘና የሚያካሄድበትን ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገና አደረጃጀቱንም ለዚህ በሚያመች መልኩ ያላዋቀረ መሆኑ፣
- የመንግስት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በተለይ 70/30 ተግባራዊ በሚደረግባቸው በምህንድስና፣ በሳይንስና በሕክምና ዘርፎች ያሉ ቤተሙከራ ክፍሎቹ በአብዛኛው ለዘርፉ አስፈላጊ በሆኑ መሳሪያዎች (የሪኤጀንት፣ የኬሚካል፣ የመለዋወጫ እቃዎች) በበቂ ሁኔታ አለመኖራቸው፣ ላብራቶሪዎችና ላይብረሪዎች ኤጀንሲው ካስቀመጠው ጥመርታ መሰረት መሆኑን የማያረጋግጥ መሆኑ፣
- ኤጀንሲው ባደረገው ተቋማዊ የጥራት ኦዲት የተገኙ ግኝቶች ላይ ማስተካከያ እርምጃ ባለመወሰዱ ችግሮቹ ያልተቀረፉ መሆኑ እና በማያሻሽሉት ተቋማት ላይ ኤጀንሲው ምንም አይነት ዕርምጃ ያልወሰደ መሆኑ፣

- ኤጀንሲው በሁሉም የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የቤተመጽሐፍት እና የቤተሙከራ አገልግሎት ደረጃውን የጠበቀ አቅርቦት መኖሩን የማያረጋግጥ መሆኑ፣
- ኤጀንሲው በሁሉም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች አመቺ የሆኑ መሠረተ ልማቶችና ሌሎች አገልግሎቶች የተሟሉ መሆናቸውን እና ተቋማቱ የሚሰጡት አገልግሎት ፍላጎታቸውን ግምት ውሰጥ ያስገባ መሆኑን የማያረጋግጥ መሆኑ፣
- አስተማሪዎች በተማሪዎች የሚመዘኑበት ወቅት የሚያቀርቧቸው ቅሬታዎች በአግባቡ የሚስተናገድበት አሠራር አለመኖሩ ትክክለኛ የተማሪዎ አካዳሚክ ውጤት ላይ ተጽዕኖ መፍጠሩ፣
- ኤጀንሲው በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚመደቡ የማስተማር ስልጠና የወሰዱ መሆናቸውን ኤጀንሲው የማያረጋግጥ መሆኑ፣
- ኤጀንሲው የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጥራትን በተመለከተ የሚከናወኑ የጥናትና ምርምር መረጃዎችን በመሰብሰብና በማቀናበር ለሚመለከታቸው ተቋማት የማያሰራጭ መሆኑ፣
- ኤጀንሲው የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚመለከቱ መረጃ አጠናቅሮ የማይዝ መሆኑ እንዲሁም ከባለድርሻ አካላት ጋር በቴክኖሎጅ የታገዘ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ የማያደርግ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

62. ስለሆነም በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ድክመቶችና ችግሮች ለማስወገድ ወይል ለማቃለል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል፡፡

# ክፍል አራት

# የማሻሻያ ሃሳቦች

63. ኤጀንሲው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የትምህርት ጥራት ተግባርን ለማከናወን የአሰራር ስርዓት በቁጠባ፣ ብቃት ባለውና ውጤታማ ለማድረግ ያስችላሉ ያልናቸውን የሚከተሉትን የማሻሻያ ሃሳቦች አቅርበናል፡-

- ኤጀንሲው የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የምሩቃኖቻቸውን መዳረሻና የቀጣሪዎቻቸውን እርካታ በማጥናት ከጥናቱ ያገኙትን ግብረ-መልስ እንደ ግብዓት በመጠቀም ሥርዓተ ትምህርታቸውን የሚያጎለብቱበትንና የሚያሻሽሉበትን እንዲሁም ከአገሪቱ ፖሊሲና ስትራቴጂዎች ጋር የሚገናዘብ መሆኑን በማረጋገጥ ለሀገሪቱ ሁለንተናዊ እድገት የሚፈለጉ ብቁ ዜጎችን ማፍራቱን የሚከታተልበት የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የመጀመሪያ ዲግሪ ትምህርት በሀገር አቀፍ ደረጃ የተቀረፁትን የትምህርት ፕሮግራሞች (curriculum) ተግባራዊ መሆናቸውን ተገቢውን የንድፈ ሀሳብ ትምህርቱንም ሆነ የተግባር ትምህርት አጠናቀው በተተመነው ሰዓት መሰረት ተምረው መመረቃቸውን፣ ተመርቀው የሚወጡ ተማሪዎች የሙያ ብቃት ምዘና የሚከናወንበትን የሚያረጋግጥበት የአሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ተፈላጊው ዕወቅትና ክህሎት ያላቸው ዜጎች እየተመረቁ መሆኑን ሊያረጋግጥ፣ ይህንንም የሚረጋግጥ ውስጣዊ አደረጃጀት ሊዘረጋ ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው በሁሉም የመንግስት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ የሚኖረው የመማር ማስተማር ሁኔታ በክፍል ውስጥም ሆነ በተቋም ግቢዎች ውስጥ ተማሪዎችን ለመማር የሚያበረታታ መሆኑን፣ በየዘርፎች የሚያስፈልጉ ቤተሙከራዎች፣ መመሪያ ክፍሎቹ አስፈላጊ በሆኑ መሳሪያዎች (የሪኤጀንት፣ የኬሚካል፣ የመለዋወጫ እቃዎች) ተሟልተው የመማር ማስተማሩ ሂደት እየተካሄደ መሆኑን፣ ለየትምህርት ዘርፉ የሚያፈልጉ መማሪያእና አጣቃሽ መጽሐፍት ለተማሪዎቹ በበቂ ሁኔታ መኖራቸውን፣ እነምዲሁም የቤተ መጽሐፍቱም ሆነ የቤተ ሙከራዎቹ ሥፋት ኤጀንሲው ባስቀመጠው የተማሪ- ቤተሙከራ/ ቤተ መጽሐፍት ጥመርታ መሰረት መሆኑን የሚያረጋግጥበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ እና ክፍተት ባለበት ላይ ደግሞ እንዲሻሻል አስተያየት ሊሰጥና መሟላታቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡

- ኤጀንሲው በጥራት ኦዲት ሪፖርት የተገኙ ግኝቶች ላይ በሚሰጣቸው የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት መሻሻል ባላደረጉ የመንግስት ተቋማት ላይ  ከሚመለከታቸው ውሳኔ ሰጪ አካላት ጋር በመቀናጀት ተገቢውን እርምጃ ሚወሰድበትን የአሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው በሁሉም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ የሚዘረጉ መሰረተ ልማቶችም ሆኑ ሌሎች አገልግሎቶች  የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ሁኔታ እና ፍላጎታቸውን ግምት ውሰጥ ያስገባ መሆኑን በማረጋገጥ በመማር ማተማሩ ሂደት እኩል ተጠቃሚ መሆናቸውን የሚረጋግጥበት የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው መምህራን የተማሪዎች የአካዳሚክ ውጤት ምዘናና የምዘና ውጤቶችን አስመልክተው እንዲሁም አስተማሪዎች በተማሪዎች የሚመዘኑበት ወቅት የሚያቀርቧቸው ቅሬታዎች ትኩረት ተሠጥቷቸው በጥንቃቄና በአፋጣኝ መፍትሔ የሚያገኙበት አሰራር በየትምህርት ተቋማቱ ተዘርግቶ ግልጽ እና ፍትሃዊ የምዘና ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን የሚያረጋግጥበት የአሰራር ስርዓት ሊኖረው ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚመደቡ አስተማሪዎች የማስተማር ክህሎት ሥልጠና መውሰዳቸውን፣ በየቤተ ሙከራው የሚመደቡ ባለሙያዎችም ለተመደቡበት ሥፍራ ተገቢው ክህሎት ያላቸውና በየጊዜው ከሚመጡ መሳሪያዎች እና አሰራሮች ጋር የሚተዋወቁበት አሰራር በየተቋሞቹ መዘርጋቱን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡
- ኤጀንሲው የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የመጀመሪያ ዲግሪ ትምህርት ጥራትን በተመለከተ የሚከናወኑ የጥናትና ምርምር መረጃዎችን በመሰብሰብና በማቀናበር መረጃዎችን ሊይዝ፣ ለሚመለከታቸው ተቋማት እና መረጃዎቹን ለሚፈልጉ አካላት የሚያሰራጭበት የአሰራር ሥርዓት ሊኖረው ይገባል፡፡ በተጨማሪም የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን የሚመለከቱትን መረጃዎ አጠናቅሮ መያዝ አለበት። እንዲሁም ከባለድርሻ አካላት ጋር በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ ወቅቱን የጠበቀና ቀልጣፋ የሆነ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል።

በመጨረሻም በከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ ፣ በኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩ ደብረማርቆስ ፣ በባሕርዳር እና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሥራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች ስላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

## አባሪ 1፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርት

| የኦዲት ጉዳይ<br>Audit issue | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት<br>Evaluative Criteria |
|---|---|
| I. የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጥራትና ደረጃቸውን የጠበቁ የመጀመሪያ ዲግሪ ትምህርት ቀርጸው ተገቢውን ግብዓት በማሟላት ቀጣይነት ያለው ትምህርት እየሰጡ መሆናቸውን መገምገም | 1. ኤጀንሲው ሁሉም የመንግስት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የመጀመሪያ ዲግሪ ትምህርት በፖሊሲ የሚመራ የውስጥ የጥራት ማረጋገጫ ተግባራዊ ማድረጋቸውን ክትትል እና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 2. ኤጀንሲው የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የመጀመሪያ ዲግሪ የትምህርት ጥራት ስታንዳርድ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡ |
| | 3. የተዘጋጀው ስታንደርድ ስራ ላይ መዋሉን ክትትል እና ቁጥጥር ማድረግ አለበት |
| | 4. የትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ስታንዳርድ መሠረት ለመተግበር በየደረጃው ያለውን ፈጻሚና አስፈጻሚ አካላትን አቅም ማሳደግ ይኖርበታል፡፡ |
| | 5. ኤጀንሲው ፖሊሲ፣ ደንብና መመሪያዎቹ ሲያዘጋጅ ተቋማት እና የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| | 6. የወጡት ደንብና መመሪያዎች ለሚመለከታቸው አስፈጻሚና ባለድርሻ አካላት ሊሰራጭና ወጥ በሆነ መልክ ተግባራዊ መደረጉን ሊከታተል ይገባል ፡፡ |
| | 7. ኤጀንሲው የማንኛውም የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የመጀመሪያ ዲግሪ ትምህርት ውስጣዊ የጥራት ማጎልበቻ ሥርዓት ዘርግተው ተግባራዊ ማድረጋቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |
| | 8. ኤጀንሲው በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የአካዳሚክ ሰራተኞች የሙያ ልማትን የትምህርት ይዘትን የመማር ማስተማር ሂደትን የተማሪዎች ምዘናና ውጤት አሰጣጥን ያካተተ ግልፅ የጥራት መለኪያ አዘጋጅተው ተግባራዊ ማድረጋቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፣ |
| | 9. ኤጀንሲው በሁሉም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ላይ እኩል ተፈፃሚነት ያለው ወጥ የሆነ የጥራት ማረጋገጫ መስፈርት ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡ |
| | 10. የተዘጋጀው መስፈርት መሰረት ተግባራዊ መሆኑን ሊከታተል ይገባል፡፡ |
| | 11. ኤጀንሲው የተቋም የጥራት ማጎልበቻ ሥርዓትን የሚመለከቱ ዝርዝር ጉዳዮች በየተቋማቱ የውስጥ ደንብና መመሪያዎች ላይ መካተቱን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |


| | |
|---|---|
| | 12.ኤጀንሲው የመንግሥት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መረጃን በዳታቤዝ በየካታጎሪ በመያዝ መረጃው በሚፈለግበት ጊዜ በቀላሉ ለማግኘት የሚያስችል ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 13.ኤጀንሲው የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በሀገር አቀፍ ደረጃ የቀረፁትን የትምህርት ፕሮግራሞች (curriculum) ተግባራዊ ማድረጋቸውን ሊያረጋግጥ |
| | 14.ኤጀንሲው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን የጥራት ደረጃ ለመስጠት በየትምህርት ክፍሉ ሊያሟሉ የሚገባቸውን አነስተኛውን ደረጃ ሊያወጣ ይገባል፡፡ |
| | 15.በወጣው ደረጃ መሰረት ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ አለበት |
| | 16. ኤጀንሲው የጥራት ማረጋገጫ ዘዴና መስፈርቶችን ከዓለም አቀፍ ተሞክሮዎች አንፃር በመቃኘትና በማጣጣም ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 17.ኤጀንሲው ለእያንዳንዱ የመንግስት ተቋም ስለሚሰጥ የጥቅል በጀት ምደባ ሃሳቡን ሊያመነጭና የጥቅል በጀት ምደባ አፈፃፀሙን ሊከታተል ይገባል፡፡ |
| | 18.ኤጀንሲው ለሚመድባቸው ለጥራት ኦዲተሮች ቀጣይነትና ወቅታዊነት ያለው ተገቢውን ስልጠና በመስጠት ሊያሰማራቸው ይገባል ፡፡ |
| | 19.ኤጀንሲው በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የጥራት ኦዲት ሊያካሂድ ይገባል፡፡ |
| | 20.የጥራት ኦዲት አካሂዶ የሰጠውን የመፍትሄ ሀሳቦች እና ማሻሻያዎች ተቋማት ተግባራዊ ማድረጋቸውን የሚከታተልበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ |
| | 21.ኤጀንሲው የጥራት ደረጃዎችን ለማሻሻል የሚረዱ ጥናትና ምርምሮች ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 22.ኤጀንሲው የከፍተኛ ትምህርት ምሩቃን የሙያ ብቃት ምዘና የሚያካሄድበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ |
| | 23. የተዘረጋው ስርዓት መሰረት ለሀገሪቱ ሁለንተናዊ እድገት የሚፈለጉ ብቁ ዜጎችን በምዘና ማፍራት አለበት፡፡ |
| | 24.ኤጀንሲው፤ በሁሉም የመንግስት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ የሚኖረው የመማር ማስተማር ሁኔታ በክፍል ውስጥም ሆነ በተቋም ግቢዎች ውስጥ ተማሪዎችን ለመማር የሚያበረታታ መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |
| | 25..ኤጀንሲው በመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎች ውሰጥ ለየትምህርት አይነቱ |

| | |
|---|---|
| | በተዘጋጀው ካሪኩለም እና ሰዓት መሰረት እየተማሩ መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፤፤ |
| | 26. ኤጀንሲው፣ ምዘናና የምዘና ውጤቶችን አስመልክተው ተማሪዎች የምያቀርቧቸው ቅሬታዎች ትኩረት ተሠጥቷቸው በጥንቃቄና በአፋጣኝ መታየታቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፤፤ |
| | 27.ኤጀንሲው የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጥራትን በተመለከተ የሚከናወኑ የጥናትና ምርምር መረጃዎችን በመሰብሰብና በማቀናበር ለሚመለከታቸው ተቋማት ሊያሰራጭ ይገባል፡፡ |
| | 28.በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚመደቡ አስተማሪዎች የማስተማር ክህሎታቸው እንዲዳብር ስልጠና በተቋሞች መሰጠቱን ኤጀንሲው ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |
| II. **የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ የተጣለባቸውን ኃላፊነት በአግባቡ እንዲወጡ ኤጀንሲው የውስጥ የጥራት ቁጥጥር እንዲያደርጉ አስፈላጊ መረጃ መስጠቱን እና ተቋማት አውቀው ተግባራዊ እንዲያደርጉ አስፈላጊው ድጋፍ ማድረጉን መገምገም** | 29.ኤጀንሲው ማንኛውም የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የጥራት ችግር በሚከሰትበት ጊዜ ተጠያቂ የሚሆኑበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል፡፡ |
| | 30.ኤጀንሲው በሁሉም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የሚሰጠው አገልግሎት ፍላጎታቸውን ግምት ውሰጥ ያስገባ መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |
| | 31.ኤጀንሲው በሁሉም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ቤተ መጽሐፍት አገልግሎት ደረጃውን የጠበቀ አቅርቦት መኖሩን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ |
| | 32. ኤጀንሲው በሁሉም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚሰጠው የቤተ ሙከራ አገልግሎት ደረጃውን የጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ |
| III. **ኤጀንሲው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ ከውጪም ሆነ የውስጥ ባለድርሻ አካላት ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሠራር ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ** | 33.ሚኒስቴሩ ማዕከሉና ኤጀንሲው የምሩቃንን የብቃት መመዘኛዎችን ሀገራዊ የምሩቃን ብቃት ማዕቀፍ አማካኝነት ተቋማቶች የሚሰጡት የትምህርት ጥራት የሚሻሻልበትን ስርዓት ቀርፀው በቅንጅት ሊሰሩ ይገባል፡፡ |
| | 34.ትምህርት ሚኒስቴር/ የትምህርት ጥራትና ማረጋገጫ ኤጀንሲ በቅንጅት ለሚያወጣቸው የጥራት መስፈርቶችና የተለያዩ መመሪያዎች ተቋማት ተግባራዊ የሚያደርጉበትን ስርዓት ዘርግቶ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርጉ ይገባል:; |
| | 35.ኤጀንሲው የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የምሩቃኖቻቸውን መዳረሻና የቀጣሪዎቻቸውን እርካታ በማጥናት ከጥናቱ ያገኙትን ግብረ-መልስ እንደ ግብዓት በመጠቀም ሥርዓት ትምህርታቸውን የሚያጎለብቱበትንና የሚያሻሽሉበትን ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ |

| | |
|---|---|
| | መሆኑን ሊከታተል ይገባል |
| | 36. ኤጀንሲው ከተቋማት እና ካሉት ባለድርሻ አካላትም ጋር መረጃዎችን በፍጥነት ለማሰራጨትም ሆነ ለመቀበል በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የአሰራር ስርዓት ሊኖረው ይገባል፡፡ |
| | 37. ኤጀንሲው አህጉራዊ ከሆኑ መሰል ተቋማት ጋር በቅንጅት በመስራት የልምድ ልውውጥ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |

Office of the Federal Auditor General

# አባሪ ሁለት፡ ድርጅታዊ መዋቅር



# አባሪ 3፡ የሥራ ሂደት መግለጫ

